ቀሲስ አስተርአየ (nigatuasteraye@yahoo.com)
Kansas city

ሚያዝያ ፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ/ም

# ፈር የለቀቀ ቁምስና በቤተ ክርስቲያን ላይ የተደቀነ አደጋ

ፍጥረት ሁሉ ቦታውንና መስመሩን ከጠበቀ ለቦታውና ላካባቢው ተስማሚና ቅዱስ ነው:: በአንጻሩ ያለቦታው የሚውል ነገር ሁሉ ተቃራኒና አፍራሽ ነው:: የአገር ፍቅር ሳይኖራቸው የሕዝብ ክብር ሳይሰማቸው አገር በሚገለገልበት ሕዝብ በሚከበርበት በመንግሥትና በመሳሰሉት መዋቅሮች የተሰለፉት ሰወችም የሕዝቡን ክብር ስለማይጠብቁ ለድንበር ለታሪክ ለባሕልና ለእምነቱ ስለማይጠነቀቁ ሕዝቡ ከጥላቻው የተነሰ ታሪክ አደፍራሾችና ድንበር አፍራሶች አርጎ በመመልከት ይጸየፋቸዋል:: በቤተ ክርስቲያናችንም ነገረ መለኮቱን ሳያውቁ እየቆመሱ እየመነኮሱና፥ እየጳጳሱ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመግባት የቤተ ክርስቲያኒቱን ኦርቶዶክሳዊ ሥርአተ ትምሕርት፥ ነገረ መለኮትና፥ መንፈሳዊ አቋም እያበላሹ፥ የተሰጣቸውን የክህነት ማእረግ ለወንበር መንጠልጠያና ለገንዘብ ማግበስበሻ የሚያውሉትንም፥ የነገረ መለኮቱ አደፍራሾች ለቤተ ክርስቲያን ውድቀት የተደቀኑ አደጋወች አድርጎ ሕዝበ ክርስቲያኑ ይመለከታቸዋል::

## ለመሆኑ ቁምስና ምንድን ነው?

ቁምስና በግእዙ ቋንቋ ተሰውሮ ከምንኩስና በስተ ጀርባ ሆኖ፥ ብዙ የሚባልለት ነገር ስላልነበረ እንደ ምንኩስናው በአገራችን ተብራርቶ አይታወቅም:: ቃሉ መጀመሪያ ብቅ ያለው በግሪኮች አካባቢ ነው:: ከብዙ ነገሮች ጋርም የተያያዘ ነው:: በጥንታውያን ግሪኮች መካከል ይኖሩ የነበሩ ጣዖት አምላኪ ቡድኖች ተለይተው የሚጠሩበት የመታወቂያ ስማቸውም ነበር:: ከሌላም እንዳገኘሁት አሳብ ከሆነ በሰርግ ላይና ልዩ በሆኑ በአሎች እየተገኙ በመጠጥ ኃይል እየተገፉ የሚዘፍኑ ቡድኖች ነበሩ ይላል::(http://en.wikipedia.org/komos) ሌላው ሐሳብ የባዛንታይን ቤተ ክርስቲያን መነኮሳት ጸጉራቸውን አይላጩም ነበርና ለጸጉራቸው ማበጠሪያና ማሰሪያ የሚጠቀሙብትን ነገር ይጠሩበት ነበር::
(htt://www.orthodoxwiki.org/ Igumen) የእንግሊዘኛው መዝገበ ቃላትም comose ይለዋል::

የበለጠ ሲገልጸው ደግሞ downy ብሎታል:: ይህም በረዥሙ ወደታች የሚወርደውን ጸጉር ያሳያል:: ወደታች የሚንጠለጠል ጭራ ወይም ጣት የመሰለ ነገር ያለው ቁስ-አካል ማለት ነው:: ከአገጭ ወደታች የሚወርደው ጺምም በዚህ ገለጻ እንደሚካተት መገንዘብ ይችላል:: የባዛንታይን መነኮሳት የኮመሳቸውን (ጸጉራቸውን) ርዝመት ለረዥም የምንኩስና ዘመናቸው እንደ ምልክት ይጠቀሙብት ነበር:: አባቶች "ውሀን ከጥሩ ነገርን ከስሩ" እንዲሉ ቃሉ ከየት መጣ ብሎ ለሚጠይቅ ፍንጭ ለመስጠት ርቄ ወደ ሌላው ባሕል ገባሁ እንጅ መከተልና መያዝ ያለብን አባቶቻችን ተርጎመው ያስቀመጡልን መሆን እንዳለበት ሁላችንም የምንስማማበት ይመስለኛል::

"ቆሞስ" የሚለው ቃል አተረጓጎሙ መጀመሪያ ብቅ ባለበት አካባቢ ከላይ እንደተገለጸው ሆኖ ሳለ የግእዙ ሊቃውንት አባቶቻችን በተፈጠረበት አካባቢ ያለውን አተረጓጎምና አጠቃቀም ለኛ ስለማይጠቅም ሸልተውና ጠርበው በማስተካከል ኮሞስን በሁለት መንገድ ተርጉመው ስምና ግብር በመስጠት አስተምረውናል:: አንደኛው ትርጉሙ "በጳጳስ ማእድ ቤት ምግብ በመቀቀልና በማቅረብ የሚአገለግል" ነው:: በጳጳሱ ማእድ ቤት ቁጥራቸው ሲበዛ ደግሞ የሰጡት አገልግሎት ተገምግሞ፥ ከጳጳሱ ቆብና ሜሮን እየተቀበለ ወደገዳማቱና አድባራቱ ለሚመነኩሱ መነኩሴወች የሚያደርስ ተላላኪ ነው:: ሁለተኛ ትርጎሙ ደግሞ "ኮ"ን ወደ "ቆ" በመለወጥ "ክርስቲያኖች በቤታቸው ደግሰው ለካህናቱ የሚአቀርቡትን ድግስ በኃላፊነት ተረክቦ ካሕናቱን ከየቤታቸው የሚጠራና ምግቡን በማሳለፍ የሚአገለግል ኮሞስን "መጨኔ" ብለውታል:: አሳላፊ ማለት ነው::

*"ወከማሁ መምህራንኒ ይፈቅዱ ከመ ይኩነ አርዳኢሆሙ ሠናያነ አእምሮ ወምግባር ወተመሃርያነ ውስተ ኪነቶሙ ወይኩኑ ተመሃርያን ትሩፋነ ወመዋዕያነ ለዘይትቃወሞሙ ወበእንቲአሆሙ ይትአኮቱ መምህራኒሆሙ እስመ ዝንቱ ጽድቅ ይበጽሕ በፍጻሜ ተልእኮቶሙ::"(አንቀጽ ፲:፫፻፷፬) (፲፩)* እንዲል: ቆሞሳት በውስጣቸው የተቀመጠ መመዘኛ እውቀት ስለሌላቸው የመጀመሪያ ተልእኳቸውን ለማከናወን በተሰለፉባቸው አካባቢወች የሚመለከቷቸውና የሚሰሟቸው ነገሮች ይቀርጿቸዋል:: በወጥቤትነት የሚረዱት ጳጳስ የተማረና በመንፈሳዊነቱ የበሰለ ከሆነ፥ ከጳጳሱ የወረሱት ልምድ በገዳሙና ባካባቢው ተወዳጅ ያደርጋቸውና በጳጳሱና በገዳሙ ስምምነት በአበምኔትነት ሊአገለግሉ ይችላሉ:: በደብሩ አካባቢ በመጨኔነት የሚአገለግሉትም እንደዚሁ ሊቃውንት አበው ተጠግተው ከነሱ በመስማትና በማየት በመንፈስና በእውቀትም የበሰሉ ሆነው ከቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሳይዘዋወሩ ጸንተው ባገልግሎቱ እስከ ሽምግልና ከቆዩ፥ ሊቃውንቱ ሕዝቡ እንደ ቋሚ ሐውልት አድርገው ያከብሯቸዋል:: የጸሎት አሳራጊ ይሆናሉ:: በክህነቱ አገልግሎት ግን ፈጽመው ጣልቃ አይገቡም:: ለጸሎት አሳራጊነትና ለሊቀ ምርፋቅነት ይሰየማሉ:: ይህም የሚሆነው *"በእናንተስ እንዲህ አይደለም ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን"(ማቴ ፳:፳፯)* የሚለውን የክርስቶስን ቃል ፍትህ ነገሥቱ ወስዶ "በተልእኳቸው ፈጥነው የመታዘዝ ጸጋ ያላቸውን ባለመማራቸው ብቻ ለገዳሙ አስተዳዳሪነት ምርጫ አትለፏቸው ስለሚል ነው::: ይህም ቢሆን መመሪያው *"ወለእመ ኮነት መፍቅድ ኀበ ፍድፋዴ አዕምሮ መጻሕፍት በምክንያተ አስተርዮተ ዕልወታት ይሢምዎ ለማዕምረ መጻሕፍት" (ፍ.ነ አንቀጽ ፬: ቁጥር ፳፰-፳፱)* ስለሚል:- ዘመኑ ሃይማኖት የሚፈተንበት መናፍቃን የበዙበት ከሆነ ጠንቅቀው ነገረ ሃይማኖቱን ለተረዱት ቅድሚያ ይሰጥ ይላል:: ከዚህ ሌላ በክርስትና እምነታችን ሰውን የሚቀድሰውና የሚአከብረው የልብ ንጽሕና ለመታዘዝ ፈቃደኛ እና የመንፈስ ልዕልና ያለው እንጅ የሹመት ማእረግ የቀለም ትምህርትና ሐብት አለመሆኑን በተግባር ለማስተማር ጭምር ነበር::

አንዳንድ ጊዜ ስለነገረ መለኮት ምንም እውቀት የሌለው ሰው ወደ ጵጵስናው ይገባና ሕይወቱ ሁሉ ዓለማዊ

ይሆናል:: ይህን የመሰለ አሳዛኝ እድል ቆሞሳትን የሚገጥማቸው ከሆነ፥ የሚመዝኑበት በውስጣቸው የተቀመጠ እውቀት ስለሌላቸው ከሱ ያዩትን መጥፎ ባሕርይ ወርሰው እንደመመሪያ አርገው በመጠቀም ለገዳሙ አደጋ ላካባቢው ከፍተኛ ቀውስ ይሆናሉ:: በየደብሩ ያሉት ኮሞሳትም (መጨኔወች) እንዲህ የመሰለ አጋጣሚ ይገጥማቸዋል:: ለካህናቱ የቀረበውን ድግስ እየተካፈሉ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚኖሩ ለመስራትና ለመማር ሰነፎች የቤተ ክርስቲያን አባቶች "መስክ ዋሾች" የሚሏቸው ከዲያቆናቱ የሚፈጠሩ ቡድኖች አሉ:: እነዚህ "መስክ ዋሾች" ከመንደር ረኞች ከከተማው ጋጠወጦች ጋር በመግጠም በየመንደሩ እየዞሩ ያልሆነ ነገር የሚሰሩ ናቸው:: መጨኔወቹ  ከነሱ ጋር በመግጠም በደጀሰላሙ አካባቢና ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግር የሚፈጥሩ ይሆናሉ:: ምእመናኑ ለካህናቱ አዛጋጅተው ያመጡትን ድግስ ካህናቱ ከመምጣታቸው በፊት በጎድን ገብተው በሌላ እቃ ገልብጠው ወደ ጫካ ወስደው ይበላሉ:: በቤተ መቅደስና በቅኔ ማኅሌቱ በሚደረጉት አገልግሎቶችም ጣልቃ በመግባት ሸውክና አሉባልታ እየፈጠሩ ለሰይጣንና ለክፉ አድራጊወች መሳሪያ ይሆናሉ:: እንዲህ አይነት ኮሞሳት ሲፈጠሩ ሌላውን ከመበከላቸው በፊት ሊቃውንቱ በፍጥነት ያስተካክሏቸው ነበር:: ሕዝቡም ከሊቃውንቱ ጋር በመተባበር መስመር የሳቱትን ኮሞሳት ይገስጹ ነበር:: ተግሳጽ የማይቀበሉ ምክር የማይሰሙ ከሆኑ ላካባቢው መንፈስ ደህንነት ሲባል ተወግዘው ይለያሉ:: አበው ሊቃውንት ተርጉመውና ሰርተው ካስቀመጡት ስርአት ኩ(ቁ)ምስናው ባለመውጣቱ መስመሩን ሲስትም፥ ሊቃውንቱና ሕዝቡ በመተባበር ስለተቆጣጠሩት በአገራችን የምንኩስናውን ያህል ሳይታወቅ እስከ አሁኑ ፓትርያርክ ዘመን ድረስ ቆይቶ ነበር::

## ከ ፲፭ አመታት ወዲህ የሚታየው ቁምስናስ ምን ይመስላል?

ቁምስና ከላይ እንደ ተገለጸው ተልእኮ በማገልገል የተመዘነ የእምነት ጽናትና ትህትና የሚጠይቅና በብዙ ፈተና ለማለፍ ጊዜ የሚፈጅ ሆኖ ሳለ አሁን በሥልጣን ላይ ያሉት ፓትርያርክ እየሰየሙ የሚልኳቸው ቆሞሳት ባብዛኛው ቦታቸውን የለቀቁ ተልእኳቸውን የሳቱ ለጥፋት መጋረጃ የሆኑና በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የተደራጁ አደጋወች ናቸው:: የጉባዔው ሊቃውንት አባቶቻችን ያስተማሩንን ሳንለቅ ፕርያርኩን ስለ ሰየሚቸ ቆሞሳት እስቲ እንጠይቃቸው:: "ጳጳሳት ልትሆኑ ትንሽ የቀራችሁ ናቸሁ" እያሉ በኢሮፕና በአሜሪካ የሚልኳቸው ለየትኛው ጳጳስ አገልጋይነት ለየትኛውስ ደብር መጨኔነት ነው? ወይም በየትኛው ገዳምና ጳጳስ መካከል ቆብና ሜሮን ለማመላለስ ነው?

ከላይ እንዳልኩት ቆሞሳት በተሰለፉበት አካባቢ የጠነከረ መንፈሳዊ ምሳሌ ካላገኙ በቀር ከፊታቸው የሚአዩትን ነገር
ነጥቀው የሚሄዱ አደገኞ ናቸው:: የሚመዝኑበት ውስጣቸው የተቀመጠ  የጠለቀ መንፈሳዊ እውቀት የላቸውም:: እየሰሙና እያዩ እንደምሳሌ የሚወስዱት ከነሱ በላይ የሆነውን አካል ነው:: በመጋቢነት ያገለገለቱን ጳጳስ ወይም በመጨኔነት ያገለገሉበትን ደብር ባሕርይ ያንጸባርቃሉ:: በቆሞሳቱ የሚንጸባረቀው ከነሱ የወረሱት ነው:: የጳጳሳቱም እቅድና አላማ በቆሞሶቻቸው ባሕርይና ተግባር እየተገለጠ ነው:: "ጳጳስ ለመሆን ትንሽ የቀረው ማለት ነው" እየሉ ለቁምስና የሰጡት ትርጉም "ያች ትንሽ ነገር" ምን ትሆን? ብሎ ለሚጠይቅም መልሱን ማግኘት የሚከብደው አይመስለኝም::
የሚልኳቸው አብዛኞቹ ቆሞሳት ሲአደርጉ የሚታዩት አገር ላገር በመዞር ገንዘብ መሰብሰብና የግል ንብረት ማስቀመጥ ነው:: ሲናገሩ የሚሰሙትም በውስጣቸው የሌለውን መመጻደቅና የበረሐ ባሕታዊ የሚናገረውን አስመስሎ መናገር ውሸትና መቀላመድ ነው:: ከህዝቡ ባጭር ጊዜ ውስጥ ጠቀም ያለ ገንዘብ የሚአገኙ ከመሰላቸም የላኳቸውን ፓትርያርክ "በሥልጣን ላይ ያሉት ከክርስትና ክልል የወጡ ናቸው: ለቤተ ክርስቲያንና ለሕዝቡ ምንም የማይሰማቸው ጨካኝ ናቸው" እያሉ ለሕዝቡ ይናገራሉ:: ፓትርያርኩና ጳጳሳቱም በየዋሁ ሕዝብ ፊት ይቅርባይ መስለው ለመታየትና በዚህ ዘዴ ተሸፍነው የሚፈልጉትን "ትንሽ ቀረቻችሁ" የሚሉትን እቅድ ይፈጽማሉ:: የቆሞሳት ድካምና ፍላጎት በሚገባ ስለሚአውቁ ደኅስ ያለ ገንዘብ ወይም ደግሞ አበጥ ያለ ወንበር እያሳዩ እንደገና ወደሳቸው ይመልሷቸውና ተገልብጠው ቃላቸውን ለውጠው ሲአወግዟቸው ለነበሩት ለፓትርያርኩ ሰግደው እኛን በተዘዋዋሪ መንገድ ሊአሰግዱን ይጥራሉ:: ለመሆኑ እኔም ሆንኩ በውስጥና በውጭ ያለው ሕዝብ ስለፓትርኩ የውስጥ ደካማ ባሕርይ ምን እናውቃለን? ሁሉንስ የምንሰማው እራሳቸው ፓትርያርኩ በኢሮፕ እና ባሜሪካ ከሚልኳቸው ቆሞሳት አይደለምን?

ምን ቆሞሳት ብቻ በደርግ ዘመን ከተሰየሙት ሊቃነ ጳጳስትም ከቁጥጥር ውጭ የወጣ የመጨኔ ባሕርይ በየደረሱብት ሲአሰራጩ አይተን ታዝበናል:: ካናሳሁት ዘንድ ይቅርታ አርጉልኝና ልጨርሰው::        ባንድ ወቅት የቀድሞው  አቡነ ይስሀቅና አበነ ገብርኤል በተገኙበት በዲሲ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተሰበሰብን:: የጉባዔው ሊቀመንበር ቃለ ጉባዔውን እንድጽፍ አዘዙኝ:: የቤተ ክርስቲያኒቱን ሥርአት በመከተል ያገልግሎት ዘመን የልምድና የእድሜን ተዋረድ በመጠበቅ በጉባዔው ላይ የተገኙትን ካሕናት ተራ ዝርዝር ጻፍኩ:: ሊቀ መንበሩ የጻፍኩትን ተራ ዝርዝር አይተው "ሥርአትና ደንብ ጥሰሐልና ከዚህ ቀደም የተዘጋጀ ቃለ ጉባዔ ስላለ ያን አይተህ የካሕናቱን ቅደም ተከተል አስተካክል" አሉኝ:: ከስር የነበረውን በፊት የተዘጋጀውን ቃለ ጉባዔ ገልብጬ ሳይ፥ ወጣት መነኮሳት ቆሞስ አባ እገሌ እየተባሉ ካባቶች ሊቃውንት በላይ ተደርድረዋል:: በጣም አዘንኩ:: እጅግም ገረመኝና "ለምን እንዲህ ሆነ ? ብየ ለጠየኩት የተሰጠኝ መልስ "እንዴ! እንዴ! እነሱማ የተከበሩ ቆሞሳት ናቸው!" የሚል ነበር:: ይህ አነጋገር የቤተ ክርስቲያናችንን ሥርአት አመዝግዝጎ ለመጣል የተማሩትንና ለብዙ ዘመን ያገለገሉትንም አባቶች ሞራል ለመምታት የተዘጋጀ ደባ ምን
ያህል በየዋሐን አባቶች አዕምሮ ውስጥ እንኳ ሳይቀር እንደገባ ተረዳሁና በጣም አዘንኩ::

እዚአው ላይ አቡነ ገብርኤልን ቆሞስ ምን ማለት እንደሆነ እንዲነግሩኝ ጠየኳቸው:: ትክክለኛውን ከመመለስ ይልቅ "አንተ በድሮ በሬ እያረስክ ነው፥ ድሮ የነበረው አሁን የለም ቀርቷል" የሚል መልስ ሰጡኝ:: ቀጠሉና "ወጣቱ ሁሉ ቆቡን እያጠለቀ እራሱን ቆሞስ እያለ ቤተ ክርስቲያኒቱን ባፍንጫዋ ሊደፏት ነው:: የቀራቸው ነገር ቢኖር እኛ የምናደርገውን ሹርቤ ቆብ ማጥለቅ፥ አርዌ ብርቱን መጨበጥ ነው እንጅ ሁሉንም እያደረጉት ነው" አሉ:: እኔም ቀጠልኩና "መፍትሔው ምን ይመስለወታል? ብየ ለጠየኳቸው የሰጡኝ መልስ "አሁን በሥልጣን ላይ ያሉት ፓትርያርክ

እስካሉ ድረስ ምንም መፍትሔ የለውም" የሚል ነበር::

በዚያው አመት ያትላንታው ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አመታዊ በአሉን ያከብር ነበረና ተጋብዤ ሄድኩ:: አቡነ ገብርኤልም ለማክበር ተገኝቶ ኖሮ ቀዳሹ እሳቸው ነበሩ:: ሁለተኛ ተራዳኢ ቄስ ሆነው ከሳቸው ጋር የተሰለፉት ወጣት መነኩሴ ነበሩ:: ቅዳሴው ተጀምሮ እስኪአልቅ ድረስ አቡነ ገብርኤል የቅዳሴው መጽሀፍ "ቀሲስና ካህን" በሚለው ቦታ ቆሞስ የሚለውን በመተካት "ቆሞስ ቆሞስ ቆሞስ" በማለት ቅዳሴውን ጨረሱት:: ዲያቆኑም በበኩሉ "በእደ ገብሩ ካሕን" የሚለውን ትቶ "ሊቀጳጳስ" እያለ በመጮኸ ቅዳሴው አለቀ:: ዲሲ ላይ አቡነ ገብርኤል "ለዚህ አቅጣጫ መሳትና መበላሸት ተጠያቂው አሁን በስልጣን ላይ ያሉት ናቸው" ያሉትን ረስተው ራሳቸው ሲአደርጉት በማየቴ እጅግ ታዘብኳቸው:: ቅዳሴው አለቀና "ለበዓሉ የተዘጋጀውን ጠበልና ጸሪቅ ቅመሱ" ተብለን ካንድ ክፍል ተቀምጠን ሳለን ለምን እንዲህ እንዳደረጉ ጠየኳቸው:: "አንተ እንዲህ የመሳሰሉትን ጥቃቅን ነገሮች አይተህ እንዳላየህ ሰምተህ እንዳልሰማህ እለፈው" አሉኝ:: ከጥጋችን የተቀመጡ ሌላው ተጋባዥ ይሰሙን ስለነበረ "ቀሲስ ምን ይደንቀወታል ምንም የማያውቁትን እነ እገሌን ሁሉ ከመርካቶ ልብስ ሰፊነት እየሰበሰቡ ቆሞስ ያሏቸው እሳቸው እራሳቸው አቡነ ገብርኤል አይደሉም እንዴ! ብለው ነገሩኝ::

ይህን ሰምቼ እየገረመኝ ሳለሁ ከጥቂት ወራት በኋላ እራሳቸው አቡነ ገብርኤል "ቅዱስ ፓትርያርኩ ጠሩኝና ወደ ኢትዮጵያ መሄዴ ነው" ብለው ባደባባይ ሲአወግዟቸው ወደነበሩት ፓትርያርክ ሕዝቡን ተሰናበተው ሔዱ:: ወዲያው አዲስ አበባ እንደደረሱ ፓትርያርኩ አቡነ ገብርኤልን ለቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ዲን አደረጓቸው ተባለ:: እነዚህ ሰወች ምንድነው የሚአደርጉት? በእምነቱ፥ በሕዝቡና በአገሪቱ እየተጫወቱ ነው? የተሰማሩበትን ኃላፊነት እየተወጡ ነው? በማለት እራሴን መጠየቅ ጀመርኩ:: የዲን ተግባር መንድነው? ብየ ስለዲን መጻሕፍት ማገላበጥ ያዝኩ:: ትክክለኛ ትርጉሙ
ንም ተገነዘብኩ:: የዲንን ትርጉም የማያውቁ ወጣቶች አቡነ ገብርኤልን እያዩ ጧት የተናገሩትን ማታ በማይደግሙ ቀልማዳ ባሕርይ ባላቸው ሰወች ይመስሉታል ብየ አዘንኩ:: በእንዲህ ያለ ዲን ከሚመራ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚመረቁ ተማሪወችስ ምን እውቀትና ስነ ምግባር ይዘው ሊወጡ ይችላሉ? ይህ የሚአሳየው ቤተ ክርስቲያኗን ምንጊዜም ከማትወጣው አዘቅት ውስጥ እየከተቷት መሆኑን ነው::

የፓትርያርኩ ኃላፊነት እነዚህንና የመሳሰሉትን በረዳትነት ማሰለፍና በታላላቅ ቦታወች መንፈሳውያን ተቋማት ላይ ማስቀመጥ አልነበረም:: በቅኔውና በአገባቡ ትምህርት ቤት ባለመቆየታቸው የቁምስናን ትርጉምና ተግባር ያልተረዱትን የሰንበት ተማሪወችንም ከቆሞሳቱ ጎን በማሰለፍ ቆሞሳቱን ከሊቃውንቱ በፊት በማስቀደም የሊቃውንቱን ክብርና ማእረግ ለቆሞሳቱ በመስጠት ቁምስናን ባልተማረው ሕዝብ ጭንቅላት ላይ እንዳይነቃነቅ አድርገው እንዲሰብኩት ማድረጋቸው ነው:: በነዚህ ቆሞሳትና በሰንበት አስተማሪወች የሊቃውንቱን ሞራል ለመምታት የበቀል ርምጃ የሚወስዱ አስመስሏቸዋል::

ይህ አድራጎታቸው ሕዝቡንም እየጎዳው ነው:: አንዳንድ ከንቱ ውዳሴና መሠረተ ቢስ ዝና የሚፈልጉ ሰወች ለደካማ ስሜታቸው ቅድሚያ ስለሚሰጡ ከቆሞሶች ጋራ በመተባበር በእምነቱና በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ እየዘመቱ ነው:: አምላክ ይቅር የማይለው ትልቅ ኃጢአትና ከታሪክ ተወቃሽነት የማያመልጡት እዳ የተሸከሙ ናቸው:: ገልጸው የሚናገሩ ሊቃውንት አልቀው፥ ለእምነታቸውና ለሞራላቸው የሚጠነቀቁ ምእመናን ቁጥራቸው አንሶ ቆሞሳቱ አሁን እየፈጸሙ ያሉትን ተግባር የሚቀጥሉ ከሆነ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የተደቀነው አደጋ ቤተ ክርስቲያኒቱን ጨርሶ ባያጠፋትም የሚቀጥለው ትውልድ ለማረም እንደሚከብደው መረዳት ከባድ አይሆንም::

በቤተ ክርስቲያኑ ትምህርት የደከሙ ወጣት ምሑራኖች ያለአግባብ በቆሞሳት ስር በመሆን ከፍተኛ የሞራል ውድቀት ስለደረሰባቸው ከናት ቤተ ክርስቲያናቸው እየተሰደዱ በመውጣታቸው ቤተ ክርስቲያኒቱን ተተኪ ምሑራንን እያሳጣ ነው:: ይህና የመሳሰሉት ቤተክርስቲያኗን የገጠሟት ችግሮች ሊታረሙ የሚችሉት አቡነ ገብርኤልና ቆሞሳት በቀልማዳ አንደበታቸው "አሁን በስልጣን ያሉት ሲቀየሩ ብቻ ነው" እያሉ የተናገሩት ነው:: መፍትሔው ይህ ብቻ አይመስለኝም:: የጥንት አባቶቻችን እንዲህ የመሰለ ነገር ሲገጥማቸው "አገር ተላላ ነው ይሄዳል እንደሰው: በየበሩ ቆሞ ጀግና ካልመለሰው" የሚሉትን እናስታውስ:: ጊዜ የወለደው የጥፋት ሰው ጊዜ እስኪያስወግደው ድረስ የሚአደረገውን ዝም ብሎ መመልከት አደጋነት አለው:: ክፉ ሰወች በተፈጠሩበት ዘመን እነሱን እያጋለጡ የሕዝቡን መንፈስ በመጠበቅ አቅማቸው በፈቀደላቸው የሚጮሁ ሰወች መፈጠር አለባቸው:: ይህ ካልሆነ አጥፊወች ጊዜ እስኪለውጣቸው ድረስ እያደረጉት ያሉት ክፉ ነገር ሁሉ ላዲሱ ትውልድ ጤናማ መስሎት ስለሚቀበለው እኛ ካለፍን በኋላ ለማስተካከል ለሚጥሩት ልጆቻችን እጅግ ይከብዳቸዋል የሚል ሐሳብ ያስጨንቀኛል:: እኛ ቄሶች እዳ አለብን "ቄሱም ዝም መጽሐፉም ዝም፥ የሚለው አነጋገር ከዚህ ቀደም በዚህ መሳይ ዘመን የነበሩ ምዕመናን የተናገሩት ነው:: በልማድ የተባለ ነገር የለም:: መጻሕፍት ይገለጡ! አፎቻችንም ይከፈቱ! ሰውነታችንን ንብረታችንን ከማገዘፍ ይልቅ አዕምሯችንን ባብነቱ ትምህርት ለማገዘፍ እንጣር! ካልሆነልን ቅስናውን እንተወው! ድምጼን ከፍ አርጌ እላለሁ! ቆሞሳት ወደ ተገቢ ቦታቸው ካልተመለሱ በምዕራቡ ዓለም ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ከደረሰው መንፈሳዊ ክስረትና ውርደት በኛ የሚደርሰው እጅግ የከፋ ይሆናል:: ጀምሯልም:: ስለዚህች ቤተ ክርስቲያን ይመለከተናል የምንል ሁሉ እባካችሁ እናንብብ እንንቃ እንጠይቅ ኃላፊነትም ይሰማን! በቅዳሴውና በፍትሐ ነገሥቱ የሌለውን ቆሞሳት ነን እያሉ የሚአጭበረብሩትን ሰወች ጠይቋቸው! ባብነቱ ትምህርት ሳይበስሉ በየአውደ ምሕረቱ በሚአደርጉት ገለጻ ቆሞሳቱን ወደላይ ሊቃውንቱንና አረጋውያኑን ወደታች እየጣሉ የሚአቀርቡትን የሰንበት ሰባኪወች ከየት አመጣችሁት? እያላችሁ ጠይቋቸው ገስጿቸውም:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "በእምነቱ ጸንቶ የማይቆመውን የነፍሰ ገዳዩ የዲያብሎስ ተከታይ ነው" (ዮሐ ፰:፵፬-፵፯) የሚለውን ሰርዛችሁ፥ ለእምነቱ ግድ ሳይኖራችሁ፥ ከንቱ ስምና ዝና በመፈለግ መስመራቸውን ከሳቱ ቆሞሳት ጋራ የምትሰለፉ ምእመናንም ወዮላችሁ! ይህ ይቅርታ የሌለው በአምላክም በታሪክም የሚአስፈርድ በደልነው:: የጌታችን የመድኃኒታችን እናት ቅድስት ድንግል እመቤታችን ማርያም "ትውልድ ሁሉ ያመሰግነኛል" ባለችው መሠረት የምናቀርበው ምስጋናና ውዳሴ በእምነትና በእውነት ላይ ካልተመሰረተ ተቀባይነት የለውም:: ከዚህ ከራቀ እመቤታችንን ከጎደፈው ስሜታችን ጋራ ተባባሪ እያደረግናት ነው:: እምነቱን ሳትረዱት ኦርቶዶክሶች ነን እያላችሁ

በስሜት ከቆሞሳት ጋራ በታሪካችሁና በእምነታችሁ ላይ የምትዘምቱ ወጣቶች የምታደርጉትን አቁሙ! ስህተቱን እያየና እየሰማ እያወቀ በእምነቱ ጸንቶ በመቆም የተሳሳቱትን ከመገሰጽ ይልቅ ካጥፊወች ጋር የሚተባበር ክርስቲያን አማኝ ነኝ ሊል አይገባውም:: "ቤተ ክርስቲያን ሄጄ እንዳስቀድስ ቅዳሴው አይታጎል እንጅ ለሌላው እኔ ምን አገባኝ" የሚል አማኝ ክርስቲያንም ግዳጁን የተወጣ አይደለም:: ክርስትና በቅዳሴ ብቻ የሚያድን ቢሆን ኑሮ ጌታችን ክርስቶስ *"በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ እኔ እራሴን ስለነርሱ ቀደስኩ" (ዮሐ ፲፯:፲፱)* ያለው በበቃ መስቀሉን ባልተሸከመ ነበር:: በቅዳሴው ውስጥ በሌለ መስመሩን በሳተ ቁምስና ስም ቤተ ክርስቲያናችን ለማሽከርከር ከተሰለፉት ጎን መቆም ቤተ ክርስቲያንን ለመጣል መተባበር ስለሆነ ገሐነም የሚአወርድ እንጅ የሚአጸድቅ አይደለም::

በውስጥም በውጭም ያለን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባላት ሆይ! አሁን እየተደረገ ያለውን እስቲ እንመልከት! ቁምስና ቦታውን ጠብቆ አድጎ፥ በገዳማትና በጳጳሳት መካከል ቆብና ሜሮን በማመላለሰ እያገለገለ ነው? ወይስ ቦታውን ስቶ ወደ ከተማ በመግባት ሕዝቡን እያተራመሰና ለጥፋት መጋረጃ እየሆነ ነው? ቆመሳትን" በጅምላ በጅምላ እያከታተሉ ወደ ውጪ መላካቸውስ ምንድነው የሚያሳየን? የቁምስናው ትሩፋት ከገዳሞቻችን ሞልቶ፥ ለመላው ኢትዮጵያውያን በረከቱ ተትረፍርፎ፥ በአጉል ባህል የዘቀጠውን የምእራቡን ዓለም ለመለወጥ የተዘጋጀ ቡድን ነው? ወይስ በውጭ ያለው ሕዝብ ከአገሩ መሰደዱ ሳያንሰው ተስፋ አስቆርጦ ከተዋሕዶው ኦርቶዶክስ እምነቱ ርቆ እንዲኖር ለማድረግ ያሰቡትን በቁምሰና መርከብነት ወደ ተሰደደው ሕዝብ እንዲሻገር እየተደረገ ነው? የተዋሕዶ ክርስትና አካል የሆንክ ወገኔ ሆይ! ጠይቅ! እወቅ!
ተረዳ! መስክር! ፍረድ!

**ይቆየን!**

***ከዚህ በፊት በቤተ-ክርስቲያናችን ጉዳይ ላይ የቀረቡ ጽሑፎች፥***

***፩ እርም እናውጣ*** *http://www.quatero.net/pdf/Erim.pdf*

***፪ ይድረስ ለኢትዮጵያውያን ሊቃውንት*** *http://www.quatero.net/pdf/liqawnit_1.pdf*

***፫ ነነዌ*** *http://www.ethiomedia.com/aurora/tsome_nenewe.pdfhttp://www.ecadforum.com/files/Timiqet.pdf*

***፬ ሽምግልና*** *http://www.quatero.net/pdf/shimiglina.pdf*

***፭ ጥምቀት*** *http://www.quatero.net/pdf/shimiglina.pdf*